## ምድብ አንድ (ሙዓለ ሕፃናት)

## 31ኛ ሳምንት

## ዕርገተ ክርስቶስ

**ዓላማ**

- ❖ የክርስቶስ ዕርገት ታሪክ መማር።

**ምንባብ**

- ❖ የሐዋ.ሥ 1፣6-11

**መግቢያ**

- ❖ በዛሬው ትምህርታችን በመላእክት ስለተበሰረው የክርስቶስ ዕርገት ስንማር፣
- ❖ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ሲያርግ የነበረውን ታሪክ እንመለከታለን።

**ትምህርቱ**

- ❖ ክርስቶስ ከተነሳ በኋላ ብዙ ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ ተገልጾ፣አስተምሮአቸዋል፣ አለምን ዞረው እንዲያስተምሩና እንዲያጠምቁም አዝዞቸዋል።
- ❖ ከአርባ ቀናት በኋላም የሚሄድበት ጊዜ እንደደረሰ ነገራቸው መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸውም ቃላ ገባላቸው።
- ❖ ይህን ነገሮቸው፣ባረካቸው፣ከእነሱ ተለይቶም ከምድር ከፍ ከፍ አለ፣ ከዓይናቸው እያረቀም ደመና ጋራደው።ስለተለያቸውም አዘኑ።
- ❖ ደቀመዛሙርቱ ክርስቶስ ወደ ዐረገበት ቀና ብለው እየተመለከቱ ሳለ ሁለት መላእክት ነጫጭ ልብስ ለብሰው በአጠገባቸው ቆመው ***"ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይሄ ከናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሏቸው።"***
- ❖ ደቀመዛሙርቱ ይሄን ቃል ሲሰሙ ተደስተው በአንድነት ተመለሱ።

**ሙከራ**

1.ክርስቶስ ከተነሳ በኋላ ደቀመዛሙርቱን ያዘዛቸው ምን ነበር?

---

2.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተነሳ በኋላ ስንት ቀን ቆየ?

---

3.ጌታ ሲያርግ ደቀመዛሙርቱ ቆመው ሲያዩ መላእክት ምን ነገራቸው?

---

**መዝሙር**፡-

ሞትን ድል አድርጎ የተነሳው ጌታ (2)

ዐረገ(2) በእልልታ (4)

ይቆየን....

---

**አዘጋጅ፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ** **ግንቦት ፯ ቀን ፪፻፪ ዓ.ም**